# ኃይሉ ሻውል የአሜሪካ አምባሲ...

WEDNESDAY, 25 FEBRUARY 2009

**ኃይሉ ሻውል የአሜሪካ አምባሲ የፖለቲካ አማካሪን አነጋገሩ**

በጋዜጣው ሪፖርተር

የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ሊቀመንበር አቶ ኃይሉ ሻውል በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አማካሪ የሆኑትን ሚስተር ሚካኤል ጎንዛላስን የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም. በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡ የአሜሪካን ባለሥልጣኑ አቶ ኃይሉ ጋር ቀጠሮ የጠየቁበትን ምክንያት ሲያስረዱ መንግሥታቸው መኢአድ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት እንደሚመለከት ለማወቅ ይፈልጋል ብለዋል፡፡

አቶ ኃይሉ የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ ሲያስረዱ ከ1997ቱ ብሔራዊ ምርጫ ወዲህ የፖለቲካ ሁኔታ እየተባባሰ መጥቶ አሁን መጥፎ ደረጃ ላይ መድረሱን ገልፀዋል፡፡ የፓርቲያቸውና የሌሎችም ተቃዋሚ አባላት በገዢው ፓርቲና መንግሥት አባላት እንዲዋከቡ እየተደረጉ ከመሆኑም በላይ እንግልቱና እሥራቱ እየቀጠለ ነው፡፡ በሚዲያውና በፍትህ አካላቱ ላይ ያለውም ተፅእኖ አላቋረጠም፡፡

አያይዘውም በብሔራዊ ምርጫ ማግስት የገዢው ፓርቲና መንግሥት በምርጫው ላይ የደረሰባቸውን ሽንፈት ለማካካስ ባደረጉት ጥረት ፓርቲያቸው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር በመተባበር የጠየቀው ሰባት ሀሳቦች በገዢው ፓርቲ ተቀባይነት እስካላገኙ ድረስ ሁኔታው በጣም አስጊ መሆኑን ይቀጥላል ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የታገለላቸውና የተሰዋላቸው ነፃነት፣ ፍትህና መልካም አስተዳደር ሰፍነው ህይወቱ ተለውጦ የተደላደለ ኑሮ መኖር እንዲችል፣ ገዢው ፓርቲና መንግሥት በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እንዲፀድቁ የተደረጉት ሕጎችና ደንቦች ከአዲስ አበባ ጀምሮ በየክፍለ ሀገሩ እስከ ቀበሌ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ሁሉ ባለሥልጣኖች እንዲያከበሩት እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡

በመኢአድ እምነት እነዚህ መብቶች በገዢው ፓርቲ እና መንግሥት መታፈናቸው እስከ ቀጠለ ድረስ የኢትየጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ተለውጦ ህዝብ በሠላማዊ መንገድ የመረጠውን መንግሥት የማግኘቱ ጉዳይ ስጋት እንዳደረባቸው፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት ህዝባቸውን ማንቀሳቀስ እስካልቻሉና ገዢው ፓርቲና መንግሥት በሠላማዊ መንገድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ምርጫ የማያከብር ከሆነ መጪው ጊዜያት ጨለማ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

ሚስተር ጉንዛለስ በመኢአድ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ግምገማ ሙሉ በሙሉ የሚስማሙ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት ለኢትየጵያ ሕዝብ ደህንነት፣ ልማትና ብልፅግና ሲባል መኢአድን ጨምሮ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመግባባትና በስምምነት መሥራት እንደሚገባቸው በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡ ጨምረውም ሲናገሩ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ታላቅ ሀገር በመሆኗ አዲሱ የፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የአሜሪካ አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ የሚከተለውን መመሪያ እንደገና ለመመርመር ዝግጁ ነው ብለዋል፡፡